# በታሪካዊው ኢትዮ-አሜሪካን ትስስር

# እመርታዊ ዲፕሎማሲያዊ ድር

ከ ፀሐዬ ደባልቀው
ዋሽንግተን ዲ.ሲ.

ከአንድ ምዕተ ዓመት በላይ ያስቆጠረውና በሁለቱ አገሮች በተፈራረቁት መንግሥታት ዘመን አንዴ ጋል ሌላ ጊዜ በረድ እያለ የዘለቀው የኢትዮጵያና የአሜሪካ ዲፕሎማቲክ ዝምድና ባሳለፍነው ሳምንት ኢትዮጵያዊው የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ሥዩም መስፍንና አሜሪካዊቷ አቻቸው ሂላሪ ክሊንተን እዚሁ የአሜሪካ መናገሻ ከተማና የዓለም መዲና በሆነችው በዋሽንግተን ዲ.ሲ ተገናኝተው ነባሩን የአገሮቻቸውን መልካም ግንኙነት ወደ አዲስና ወደ ላቀ የግንኙነት እርከን ያሸጋገረና በጋራ መከባበር፣ መስማማት፣ መግባባትና በእኩልነት መርህ ላይ የተንደረከከ እመርታዊ ዲፕሎማሲያዊ ምዕራፍ አስመዝግበዋል::

ኢትዮጵያ የሰው ልጅ እትብት የተቀበረባት የሥልጣኔ እምብርትና የመላው ጥቁር ሕዝቦች የነፃነት ቀናኢነት የተጋድሎ አርአያነትና የአትንኩኝ ባይነት ገድል ህያው ሃውልት ሆና በመላው ዓለም ለሰላም ለሰው ልጅ ክብር፣ ለአርነትና ለእኩልነት፣ ለተከፈለው መስዋዕትነት ፋና ወጊ፣ ቀንዲልና አቀጣጣይ ችቦ በመሆን ከአድማስ እስከ አድማስ የተከታታይ የዓለም ትውልዶችን ቀልብ የማረከችና በተምሳሌትነት የምትጠቀስ ታላቅ ሀገር ነች::

ኢትዮጵያ (League of Nations) በመባል የሚታወቀው የዓለም መንግሥታት ኅብረት ሲቋቋም ከአንጋፋ የዓለም አገሮች አምባ ላይ አህጉራችንን አፍሪካን በብቸኝነትና በነፃነት በመወከል የተገኘች መሥራች አባል ነች:: በዚያን ጊዜ በአሜሪካ ሳንፍራንሲስኮ ከተማ በተካሄደው የዚሁ ዓለም አቀፋዊ ተቋም መሥራች ጉባዔ ላይ ኢትዮጵያ በፋሽዝምና በናዚዝም ጦስ ሳቢያ ዓለም ላይ ያንዣበበውን አይቀሬ አደጋ በእርግጠኝነት በመተንበይ የዓለም አገራት አንድ ባንድ ሰለባ ከመሆናቸው በፊት ክንዳቸውን በማስተባበር በኅብረት ጽልመቱን ከወዲሁ እንዲገፉ ጥሪ ባቀረበችበት ጊዜ በወቅቱ እብሪት ማን አህሎኝነትና ትምክህት የወጠራቸው ኃያላን መንግሥታት የኢትዮጵያን

ውትወታ ከቁብ ባለመቁጠር ጆሮ ዳባ ልበስ ብለው በማለፋቸው የኋላ  ኋላ ላይ በፈፀሙት ህፀፅ መራሩን የታሪክ ጽዋ እንዲጨልጡ የግድ ብሏቸዋል::

በLeague of Nations እግር በሁለተኛው የዓለም ጦርነት ማግስት በተተካው የእስካሁኑ የተባበሩት መንግሥታት ድርጅትም አሁንም ኢትዮጵያ በነፃነት የራሷን ብሔራዊ ባንዲራ እያውለበለበች ለአህጉራችን ለአፍሪካም በአርአያነት ቆማ ዲፕሎማሲያዊ ጮኸቷን እያስተጋባች የአህጉራችንና የሌላው ዓለም ግፉአን ሕዝቦች ከቅኝ ግዛትና ከእጅ አዙር ቅኝ ግዛት እንዲላቀቁ በግንባር ቀደምትነት ታሪካዊ ሚናዋን የተወጣች በዲፕሎማሲያዊው የዓለም መድረክ በግንባር ቀደምትነት ተጠቃሽ ሀገር ሆናለች::

በ1960ዎቹ የአፍሪካ አገሮች ቀስ በቀስ ሉአላዊ ነፃነታቸውን ሲጐናፀፉም የፖለቲካ፣ የኢኮኖሚ፣ የባህልና ማኅበራዊ ነፃነታቸውን ይበልጥ የሚያጐለብቱበትን የአፍሪካ አንድነት ድርጅትን በመመሠረት ብቻ ሳይሆን አሁንም የአፍሪካ ኅብረት ርዕስ ጽ/ቤት በአዲስ አበባ ሆኖ ኢትዮጵያ ለከፈለችው መስዋዕትነት ዋጋ ክብርና ውለታን በሚመልስ አኳኋን እስከ አሁኑ ጊዜ ድረስ ሃገራችን የአፍሪካ መናኸሪያ ሆና ቀጥላለች:: እግር በእግርም የተባበሩት መንግሥታት ለአንፀባራቂው የኢትዮጵያ ግንባር ቀደም ተጋድሎ እውቅና በመስጠት የተባበሩት መንግሥታት የአፍሪካ ኢኮኖሚ ኮሚሽን በርዕስ ከተማዋና የአፍሪካ የፖለቲካ እምብርት በሆነችው በአዲስ አበባ እንዲቋቋም አደረገ:: በመሆኑም በአሁኑ ጊዜ ኢትዮጵያ ሀገራችን ከኒውዮርክና ከጄኔቫ ከተሞች ለጥቆ ሦስተኛ ው የዓለም ዲፕሎማሲያዊ ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ ማዕከል ሆናለች::

ሀገራችን አዲሱን ልማታዊ ዲሞክራሲያዊ ሥርዓት ለመገንባት ቆርጣ ከተነሳችበት ከሁለት ዓስርተ ዓመታት ባነሰ የጊዜ ቀመርም ይኸንኑ አህጉራዊና ዓለም አቀፋዊ ዲፕሎማሲያዊ ሚናዋን በማጉላት ከፍተኛ ርብርቦሽ በማድረግ ላይ ትገኛለች:: በአፈሪካ ሠላምና መረጋጋት ሰፍኖ አገሮች የህግ የበላይነትን በተከተለ አኳኋን በሰላማዊና በሰለጠነ መንገድ ችግሮቻቸውን ይፈቱ ዘንድ የተባበሩት መንግሥታት ድርጅትንና የአፍሪካ ህብረትን በመወከል በአያሌ ሃገሮች የሰላም አስከባሪ ኃይል አሰማርታ የበኩሏን ድርሻ በመወጣት ላይ ነች::

አብዛኞቹ ኃያላን መንግሥታት የዓለም አቀፍ ሽብርተኝነትን ስጋት ባላጤኑበት በዚያን ወቅት ኢትዮጵያ  ይኸንኑ እኩይ  ስጋት በብቸኝነት በቆራጥነትና በጀግንነት በመፋለም የዓለም አቀፍ ሽብርተኝነትን አይቀሬ አደገኛ ሁናቴን በእውነት በግንባር

ቀደምትነት በተግባራዊ ተጋድሎና መስዋዕትነት ያስጨበጠች፣ ሽብርተኝነትን በዓለም አቀፍ ደረጃ ለመቋቋም በተፈጠረው ግንባር በቀጠናችን ቀዳሚውን ሥፍራ ይዛ እየታገለች እውነታውን ሌሎች እንዲቀበሉ ያስመታከት የተጋች ሀገር ናት፡፡

ኢትዮጵያ ከዚህም በላይ NEPAD በተሰኘው የአፍሪካ ኢኮኖሚያዊ ልማት ትስስር መድረክ ላይ በንቃት በአባልነት እየተሳተፈችና በሊቀመንበርነትንም እየመራች እንዲሁም በዓለም አቀፍ አምባዎች ላይ በ G8 እና በG20 የበለፀጉ አገሮች የአፍሪካን አህጉር በመወከል የአህጉሪቱን ድምፅ ከፍ አድርጋ በማስማትና የአፍሪካን ጥቅም በማንፀባረቅ ወገቧን ጠበቅ በማድረግ እየተሟገተች ሁነኛና ተገቢ ሚናዋን በመጫወት ያስመዘገበችው አኩሪ ገፅታዋ ለሌላ አለም አቀፍ መድረክ ታዳሚነትና ያልበለፀጉት ሀገሮች ጠበቃ እንድትሆን አብቅቱታል፡፡ ይኸውና የዓለምን የአየር ንብረት በሚመለከተውና በ Denmark Copenhagen ከተማ በቅርቡ በሚካሄደው ዓለም አቀፋዊ ጉባዔ ላይ የበለፀጉት ሀገሮች ለቀቀተኝንት ሳቢያ በሚነጉደው የኬሚካል ልቀት ለፈጠረው የአካባቢና የአየር ብክለት አፍሪካ ተፈጥሮአዊ አካባቢዋ እንዲያንሠራራና ቅጠልያ ልምላሜዋ ወደ ነበረበት እንዲመለስ ተገቢውን ካሣና የልማት ማካካሽ እንዲከፍሉ በተጠያቂነት መንፈስም ሁነኛ የእርምት እርምጃ እንዲወስዱ ቀዳሚዋ ተሟጋች ሆናለች፡፡

በአህጉራዊና በዓለም አቀፋዊ የዲኘሎማቲክ ክንውን ጉልህ ድርሻዋ ከአጽናፍ አጽናፍ የናኘ ሞገስና እውቅናን የተጐናፀፋቸውን ያህል በሀገር ውስጥም መንግሥት ዘመናዊና የሰለጠነ ዲሞክራሲያዊ ሥርዓት በማሰላሰል ነፃ የፍትህ አካላት፣ ነፃ ኘሬስ፣ ነፃ የገበያ ኢኮኖሚ የውጭና የውስጥ ባለሀብቶችን የሚያሳትፍ የኢንቨስትመንት መዋዕል፣ በሀገሪቱ እንዲሰፍን በማድረግ በፖለቲካዊው አምባም የሕግ የበላይነት ሁነኛ ሕጋዊ ሂደት ደረጃ በደረጃ እንዲሰርጽ ሆኖ ሕገ መንግሥታዊና ፌዴራላዊ አስተዳደር ተዘርግቶ ሀገራችን በዲሞክራሲዊ ሕጋዊ ጉዳና የመራመዱን ልምድም በተግባር ተያይዛዋለች፡፡

የሰላማዊ፣ የዲሞክራሲያዊና የሕገ መንግሥታዊ ሥርዓት መቋጫና መገለጫ መንግሥት በተዋረድ እስከ ታችኛው የሥልጣን እርከን ድረስ በሕዝብ ድምፅ፣ ይሁንታና ምርጫን እየተላበሰ የሚሾምበትና የሚሻርበት ብሔራዊ ተግባር ባለፉት የ15 ዓመታት ሙከራ ሂደት ወደ አዎንታዊ ገጽታው ባደላና ባጋደለ መልኩ ትምህርት እየወሰደበት፣ ምልዓተ ሕዝቡም የመደገፍና የመቃወም ሰብአዊና ሕጋዊ መብቱ እስከነ ሕጋዊ ዳርቻው ይዘቱ ርቀቱና ጥልቀቱ እየተገነዘበው መጥቷል፡፡

በመሆኑም በአሁኑ ወቅት ሀገራችን ለአራተኛው ብሔራዊ ምርጫሽርጉድ በምትልበት ዋዜማ ከእንግዲህ በኢትዮጵያችን የሚደረግ ምርጫና እሱን ተከትሎ የሚመጣ የሥልጣን ርክክብና ሽግግር፣ በሰላማዊ፣ በዲሞክራሱያዊ፣ ሕዝቡ አብላጫ ድምፁንና ሙሉ ይሁንታውን የሰጠው አካል ነፃ ፍትሃዊና ርትአዊ እንዲሁም በሕዝብ ዘንድ ተአማኒነትን ባተረፈ የምርጫ ሥርዓት የሚከናወን እንዲሆን በሰለጠነና ሰጥቶ በመቀበል መርህ ላይ በተመሠረተ ድርድርና መግባባት የምርጫ ሥነ ሥርዓት ደንብ በሀገሪቱ አራት ሕጋዊና ፓርላሜንታዊ የፖለቲካ ድርጅቶች አጽድቀውት ሌሎች ፓርቲዎችና ግለሰቦችም ሕዝቡም ጭምር ካጐለበተው በኋላ ለተወካዮች ም/ቤት ቀርቦ ሲፀድቅ የሀገሪቱ የምርጫ ሕግ እንደሚሆን ሂደቱ በአስተማማኝ እንደቀጠለ ነው።

ይህ በአሁኑ ወቅት ኢትዮጵያ በማካሄድ ላይ የምትገኘው ዲፕሎማሲያዊ ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያና ማኀበራዊ ሁሉን አቀፍ ውጭያዊና ውስጣዊ ውጤታማ ርብርቦሽ ሀገሪቱ በሰለጠነና ዘመናዊ የዲሞክራሲያዊ መርህን በተከተለ ሁኔታ የምታደርገውን እንቅስቃሴ የመላውን ዓለም ትኩረት መሳቡ ብቻ ሳይሆን ኢትዮጵያም ዛሬም እንደትላንቱ በዓለም አቀፍ መድረክ ተገቢውን ሚናዋን እየተጫወተች የምትገኝና ይኸንንም የሚያንፀባርቀው ከሀገሮች ጋር ያላት ዲፕሎማሲያዊ ዝምድና አፀፋዊና ተመጣጣኝ እንዲሆን የግድ ይላል።

በመሆኑም በሀገራችንና በአሜሪካ መካከል ሰሞኑን የተደረሰበትን ታሪካዊ የግንኙነት መደላድል በአሜሪካ በኩል ኢትዮጵያ በዲሞክራሲያዊ ጉዳና እየተራመደች በየአምስት ዓመቱ የሚደረገውም ፖለቲካዊ ብሔራዊ ምርጫ ዓለም አቀፍ መስፈርትን እንዲያሟላ በእውን የምትታታር አገር መሆኗ በኢኮኖሚው መስክም ከአፍሪካ አሀጉር ነዳጅ አምራች ካለሆኑት አገሮች ደቡብ አፍሪካን ተከትላ በሁለተኛ ደረጃ በፈጣን የልማትና የዕድገት ጉዳና ላይ እየተራደመች ሕዝቦቿም የተባበሩት መንግሥታትን የሚልየንየሙ ግብ፣ በንፁህ ውሃ አቅርቦት በትምህርት ረድፍ፣ በጤና መስክ መስፋፋት በገጠርና በከተማ ልማት በመንገድ በመብራትና በስልክ አገልግሎት ዝርጋታ የምር ተጠቃሚ እንዲሆኑና ወደላቀ የኑሮ ደረጃ እንዲሸጋገሩ በማድረግ ላይ ያለችውን ጥረት የተቀበለና ለኢትዮጵያ ትክክለኛ ቦታ ዕውቅናን የሰጠ በሳል የጋራ ስምምነት ነው። አሜሪካ እስካሁን ኢትዮጵያ በዓለም አቀፍ ሽብርተኝነት ተጋድሎ ጉራ የምታበረክተውን ድርሻ ተገቢውን ክብርና እውቅና እየሰጠች የዘለቀች መሆኗ ሲታወቅ የአሁኑ የጋራ ስምምነት ይኸንኑ ገፅታን ከማጠናከሩም በላይ ሀገራችን በዚህ መስክ ለምታደርገው አስተዋጽኦ ወሳኙ በሀገር ውስጥ ለራሷና ለሕዝቦቿ ጥቅም ሲባል በዋናነት በእውን

በመረባረብ ላይ ያለችበትን የልማታዊ ዲሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታ በአፀፋዊ መልኩ ያደነቀና የተቀበለ በማክበርም ይህንኑ የተቀደሰ ተግባር እንዲጐለብት የአሜሪካ ልማታዊ ድጋፍ አስፈላጊነትን በተግባር ለመተርጐም ያቀነቀነ ስምምነት መሆኑና አሜሪካ በውጭ ግንኙነቱ ረገድ ኢትዮጵያን እንደ አንድ አጋርና ወዳጅ አገር የምትቀበለው ባልተሸራረፈ ሙሉዕና በተቀናጀ መርህ ላይ የቆመ የተግባር ድጋፍም ጭምር እያደረገች እንደሆነ በጉልህ ያሳየ ታሪካዊ ክንውን ነው፡፡

ባጭሩ ስምምነቱ አሜሪካ የኢትዮጵያን ልማታዊ ዲሞክራሲያዊ ሥርዓት የመገንባት ቁርጠኝነት ሙሉ በሙሉ የተቀበለችበትና በአንፃሩም ሥርዓቱን ሙሉ በሙሉ በማክበርና በመቀበል የሁለቱን አገሮች የጋራ ጥቅም በሚያስከብር መልኩ ተገቢውን ድጋፍ የምታደርግበትን ሁኔታ ያስመረ ከእንግዲህ በቋምነገሩና በይዘቱም ሁለቱም አገሮች በጋራ የሚቆሙበት፣ ጥቃቅን ልዩነቶች ሲከሰቱም በጋራ ምክክርና ውይይት እልባት እየሰጡ በዓለም አቀፍ መድረኮች በመከባበርና በጋራ ጥቅም ላይ የተመሠረተ መርህን ተከትለው  የሚጓዙበትን አዲስ ምዕራፍ የከፈተ ነው፡፡  ይህ ምዕራፍ ኢትዮጵያ ሀገራችን ዳግም በዓለም አቀፍ መድረክ ዛሬም እንደትላንቱ ይበልጥ ታሪካዊ ቦታዋን ያረጋገጠችበና በዓለም አቀፍ ፀረ ሽብርተኝነት ተጋድሎና በዓለም ሰላም ጥበቃ በምታበረክተው ምትክ የለሽ አስተዋጽኦ ብቻ ሳይሆን ከእንግዲህ ኢትዮጵያ በአዲሱ ልማታዊ ዲሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታ ጥረቷም የአሜሪካን አጋርነትና አፀፋዊ ይሁንታን የሚያላብስትና ሀገራችን ከሰለጠነው ዓለም በስልጡን የፖለቲካ ጉዞ በዓለም የዲሞክራሲ ጐራ እየተራመደች ለመሆኗ ተጨማሪ  ዓይነተኛ ምስካሬ ነው፡፡